# በምስራቅ ወለጋ ሆሮጉድሩ ዞን ዘጠኝ ሰዎች በታጣቂዎች ተገደሉ

By wazemaradio

JUL 13, 2021




ዋዜማ ራዲዮ- በምስራቅ ወለጋ ሆሮጉድሩ ዞን ኢሙር ወረዳ ልዩ ቦታው ኢላሞ የተባለ አካባቢ ሰዎች በታጣቂዎች መገደላቸውን አካባቢው ነዋሪዎች ለዋዜማ ተናገሩ።

እሁድ አመሻሽ ላይ “የኦነግ ሸኔ” ናቸው ያሏቸው ታጣቂዎች ወደ አካባቢው መተው ተኩስ እንደከፈቱባቸው የተናገሩት የአካባቢው ነዋሪዎች በወቅቱ የመንግስት የፀጥታ አካላት በቦታው አልነበሩም ብለዋል። ታጣቂዎቹ አምስት ወንዶችና አራት ሴቶች በድምሩ ዘጠኝ ሰዎችን በጥይት እንደገደሉ ሌሎች ስድስት ሴቶች ላይ ከፍተኛ ጉዳት መድረሱን ለዋዜማ ሪፖርተር ተናግረዋል።

ነዋሪዎቹ እንደሚሉት ታጣቂዎቹ አራት ህፃናትን ከአካባቢው ይዘው ተሰውረዋል ። የሟቾቹ አስከሬን ትላንት ተነስቶ ስርዓተ ቀብራቸው መፈፀሙንም ሰምተናል።

ነዋሪዎቹ እንደሚሉት የአካባቢው ሚሊሻና ልዩ ሀይል ባለመኖሩ ለጥቃት ተጋልጠናል ባይ ናቸው።
መልክአ ምድሩ ሸለቆ እና ጫካ እንደሆነ የተናገሩት የአካባቢው ነዋሪዎች ታጣቂዎቹ የመንግስት የፀጥታ አካላት በቦታው አለመኖራቸውንና ጨለማን ተገን አርገው በተደጋጋሚ ግድያና ዘረፋ እያደረሱብን ነው ሲሉ ተነገረዋል ።

የኦሮሚያ ፖሊስ በጉዳዩ ላይ መልስ እንዲሰጠን ጠይቀን በጉዳዩ ላይ መረጃ እያሰባሰበ መሆኑን ገልፆ ከሁለት ቀናት በኋላ መልሰን እንድንጠይቅ ነግሮናል። [ዋዜማ ራዲዮ]

CATEGORIES

About Wazema
Art and Culture
Benegerachin Lay-Discussion
Book Review
Current Affairs
Fake News alert
Home
Letter From Addis
News
PODCASTS
Talking points
Uncategorized
Video
Wazema Dossier
Wazema Forum

WAZEMA MEDIA

Wazema Media is legally registered organization founded in 2014 by Ethiopian exiled journalists, currently based in Addis Ababa, Ethiopia.